UDI

# የፖለቲካ ጥገኝነት ጠይቀው የአዎንታ መልስ ላገኙ ወላጆች የተጠናቀረ መረጃ
# Amharisk

## የተሰጠውን ፈቃድ የሚመለከት መረጃ

ለሴቷ ልጅዎ በኖርዌይ ጥበቃ ታገኝ ዘንድ የተፈቀደላት UDI (የውጪ ዜጎች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት) ወደ አገር ቤት እንድትመለስ ብትደረግ በፆታዊ አካል ላይ ለሚፈጸም ጉዳት (ግርዛት) ትጋለጣለች የሚል ግንዛቤ ስላለው ነው። ፈቃዱ የተሰጠው ሴት ልጅዎት ለግርዛት እንዳትዳረግ ጥበቃ እንዲደረግላት ነው።

ሴት ልጅዎ ለግርዛት እንዳትዳረግ ዋናውን ኃላፊነት የሚሸከሙት እርስዎ ኖት። ሴት ልጅዎ ተገርዛ ከተገኘች የኖርዌይ የመኖሪያ ፈቃድዎትን ሊነጠቁ ይችላሉ።

የተሰጠዎት የመኖሪያ ፈቃድ ለአንድ ዓመት ነው የሚቆየው። ይህ እንዲታደስልዎ ከማድረግዎ በፊት ወደ UDI መጥተው ሴት ልጅዎ ስለምትገኝበት ሁኔታ ከእኛ ጋር መነጋገር ይኖርብዎታል።

## በኖርዌይ አገር የምትኖር አንዲት ሴት ልጅ ለግርዛት ብትዳረግ ሊደርስ የሚችለው ነገር ምንድን ነው?

በኖርዌይ አገር ሴት ልጆችን መግረዝም ሆነ እንዲገረዙ ማድረግ በሕግ የተከለከለ ነው። ክልከላው ማንኛውንም ዓይነት የሴት ልጅ ግርዛትን ይመለከታል። በኖርዌይ አገር የሚኖሩ ሰዎች አንድ ሴት ልጅ እንድትገረዝ በማድረግ ረገድ ድርሻ የሚኖራቸው ከሆነ እስከ 10 ዓመት በሚደርስ እስራት ይቀጣሉ። ወላጆች ሴት ልጃቸው እንዳትገረዝ ማድረግ ሲችሉ ተገርዛ ከተገኘች ቅጣት ይበየንባቸዋል። ግርዛቱ በሌላ አገር ውስጥ የተከናወነ ቢሆንም እንኳን ቅጣቱ ተግባራዊ ይሆናል።[1]

እንደዚህ ዓይነት ቅጣት የተቀበሉ ሰዎች ከኖርዌይ አገር ሊባረሩ ይችላሉ።[2]

## በኖርዌይ አገር ሴቶች ልጆች ለግርዛት እንዳይዳረጉ ጥበቃ የሚያደርገው ማን ነው?

አንድ ሴት ልጅ የመገረዝ አደጋ ውስጥ መሆኗን የሚያመላክት መረጃ ካላቸው በኖርዌይ አገር ብዙዎቹ የመንግሥት እና የግል ሠራተኞች ለፖሊስ እና ለየሕጻናት ጥበቃ አገልግሎት (Barneverntjeneste) የማሳወቅ ግዴታ አለባቸው። ሳያሳውቁ ጉዳዩን ቸል ብለው የሚያልፉ ከሆነ የእስር ወይም የገንዘብ ቅጣት ይበየንባቸዋል።

የሕፃናት ጥበቃ አገልግሎት ክፍል አንዲት ሴት ልጅ ለግርዛት አደጋ የተጋለጠች ስለመሆኑ መረጃ ሲደርሰው የልጅቱን የአስተዳደግ ሁኔታ ይመረምራል። የሕፃናት ጥበቃ አገልግሎት ክፍሉ ልጅቱ ለሕክምና ምርመራ ወደ ሆስፒታል እንድትወሰድ ሊወስን ይችላል።

የሴት ልጅ ግርዛት ከሚከናወንባቸው አገሮች የመጡ ወላጆች ከአንድ የሕብረተሰብ ጤና ነርስ (helsesøster) ጋር ግርዛትን አስመልክቶ የሀሳብ ልውውጥ እንዲያደርጉ እድል ይሰጣቸዋል። በመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ሴት ልጆችም ከአንድ የሕብረተሰብ ጤና ነርስ ጋር ስለ ግርዛት እንዲነጋገሩ እድሉ ይሰጣቸዋል።

## የጤና እርዳታን የሚመለከት መረጃ

ብዙዎቹ ልጃገረዶች እና ሴቶች ወደ ኖርዌይ ከመምጣታቸው በፊት የተገረዙ ናቸው። ተገርዞ መገኘት በራሱ ክልክል አይደለም። ሆኖም ግን ወላጆች ግርዛት የተፈጸመባቸው ሴት ልጆቻቸው አስፈላጊ የሆነ የጤና እርዳታ እንዲያገኙ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው። በእያንዳንዱ የኖርዌይ የጤና ክልላዊ መዋቅር ስር ግርዛት ለተፈጸመባቸው ልጃገረዶች እና ሴቶች የጤና እርዳታ የመስጠት የተለየ ኃላፊነት የተጣለበት የሴቶች ክሊኒክ ይገኛል።

ተጨማሪ መረጃ የሚያስፈልግዎ ከሆነ የግዴታ ጋብቻን እና ግርዛትን በሚመለከት ለቀይ መስቀል በስልክ ቁጥር 815 55 201 መደወል፣ ወይም ከሀኪም እና ከሕብረተሰብ ጤና ነርስ (helsesøster) ጋር መነጋገር፣ ወይም በሚኖሩበት ከሙኑ ከሚገኘው የሕጻናት ጥበቃ አገልግሎት ጋር መገናኘት ይችላሉ። እንዲሁም በ www.nkvts.no ድህረገጽ ላይ ስለ ግርዛት እና የጤና እርዳታ አገልግሎትን የሚመለከት መረጃ ያገኛሉ። በተጨማሪም በተለያዩ ቋንቋዎች የተዘጋጁ በራሪ ጽሁፎች በዚህ ድህረገጽ ላይ ያገኛሉ።

---

1 Lov om forbud mot kjønnslemlestelse (ግርዛትን የሚከለክለው ሕግ) § 1

2 Utlendingsloven §§ (የውጪ ዜጎች ሕግ) 66-68

UDI

# Informasjon om kjønnslemlestelse
# Norsk

## Informasjon om tillatelsen

Datteren din har fått beskyttelse i Norge, fordi UDI mener at hun står i fare for kjønnslemlestelse (kvinnelig omskjæring) ved retur til hjemlandet. Tillatelsen er gitt for å beskytte datteren din mot omskjæring.

Det er du som har hovedansvaret for at datteren din ikke blir omskåret. Dersom datteren din blir omskåret kan du miste oppholdstillatelsen din i Norge.

Oppholdstillatelsen din varer i ett år. Før du kan få fornyet den, må du komme til UDI for å ha en samtale med oss om situasjonen for datteren din.

## Hva skjer hvis jenter som bor i Norge blir omskåret?

I Norge er det forbudt å utføre eller medvirke til kjønnslemlestelse (kvinnelig omskjæring). Forbudet gjelder alle former for kvinnelig omskjæring. Personer som bor i Norge kan bli straffet med inntil ti års fengsel, dersom de medvirker til at en jente blir omskåret. Foreldre kan bli straffet dersom datteren deres blir omskåret og det hadde vært mulig for dem å avverge omskjæringen. Det gjelder selv om omskjæringen skjer i et annet land.[1]

Personer som får slik straff kan bli utvist fra Norge.[2]

## Hvem passer på at jenter i Norge ikke blir omskåret?

Mange offentlig og privat ansatte i Norge har plikt til å informere politiet eller barnevernstjenesten hvis de har opplysninger om at en jente kan stå i fare for å bli omskåret. De kan bli straffet med bøter eller fengsel, dersom de lar være å varsle.

Når barnevernstjenesten får melding om at en jente står i fare for kjønnslemlestelse, vil de undersøke barnets omsorgssituasjon. Barnevernstjenesten kan gi pålegg om at barnet bringes til sykehus for medisinsk undersøkelse.

Foreldre fra land med kvinnelig omskjæring, vil få tilbud om samtale med helsesøster for å snakke om omskjæring. Jenter som går på ungdomsskolen i Norge vil få tilbud om samtale med helsesøster for å snakke om omskjæring.

## Informasjon om helsehjelp

Mange jenter og kvinner har blitt omskåret før de kom til Norge. Det er ikke forbudt å være omskåret, men foreldre har plikt til å påse at døtre som er omskåret får nødvendig helsehjelp. I hver helseregion i Norge finnes en kvinneklinikk som har et spesielt ansvar for å gi helsehjelp til jenter og kvinner som er omskåret.

Dersom du trenger mer informasjon, kan du ringe Røde Kors-telefonen om tvangsekteskap og kjønnslemlestelse 815 55 201, snakke med lege eller helsesøster, eller du kan kontakte barnevernstjenesten i kommunen der du bor. Du kan også finne informasjon om kjønnslemlestelse og tilbud om helsehjelp på nettsiden www.nkvts.no. Her finner du blant annet informasjonsbrosjyrer på ulike språk.

1 Lov om forbud mot kjønnslemlestelse § 1
2 Utlendingsloven §§ 66 - 68